# የውጭ ግንኙነትና የዲሎማሲያችን ዋና ዋና ስኬቶች

## 1.1. ኢትዮጵያ፣ ጎረቤት አገሮች እና ክልላዊ ትስስር

አገራችን ከኤርትራ፣ ጅቡቲ፣ ሶማሊያ፣ ኬንያ፣ ሱዳንና ደቡብ ሱዳን ጋር ከግዛት ጉርብትና ባሻገር በቋንቋ፣ በባህል፣ በታሪክ፣ በተፈጥሮ ሀብት፣ ወዘተ ተሳስራለች። ጎረቤት አገራት የአገራችን ሰላምና መረጋጋት ፣ ልማት እና ዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ሂደት ላይ ያላቸውን ከፍተኛ ሚና በመረዳት የአገራችን የውጭ ግንኙነት እና ብሄራዊ ደህንነት ስትራቴጂ በአፍሪካ ቀንድ ዘላቂ ሰላምና ልማትን ማረጋገጥና ኢኮኖሚያዊ ትብብርን ማጠናከር ላይ ያተኮረ ነው፡፡

### 1.1.1. ከጎረቤት አገራት ጋር ያለን የተናጠል ግንኙነት

ኢትዮጵያና ጂቡቲ ዘመናትን ያስቆጠረ ዲፕሎማሲያዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ግንኙነት አላቸው። ባለፉት ዓስር ዓመታት ሁለቱ ሀገሮች ሁሉን-አቀፍ ግንኙነታቸውን ወደ ኢኮኖሚያዊ ውህደት ለማሸጋገር ባስተላለፉት ውሳኔ መሰረት ከአዲስ አበባ ጅቡቲ የስታንዳርድ ጌጅ የባቡር ሐዲድ ተዘርግቷል፣ የታጁራ ወደብ ግንባታ እየተካሄደ ነው፣ የኢትዮጵያ እና ጅቡቲ የጋራ የባቡር ኩባንያ መመስረቻ ስምምነት ተፈርሟል፣ ኢትዮጵያ ለጂቡቲ የኤሌክትሪክ ሀይል በማቅረብ ላይ ትገኛለች፣ እንዲሁም ከአዲጋላ- ጅቡቲ ከተማ የሚዘረጋው ድንበር ዘለል የንፁህ የመጠጥ ውኃ አቅርቦት እየተከናወነ ነው፡፡ በተጨማሪ በመቶዎች የሚቆጠሩ ጅቡቲያውያን ወጣቶች በሀገራችን የመንግስትና የግል ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የትምህርት እድል ያገኙ ሲሆን የኢትዮጵያ እና ጂቡቲ የጋራ ሚኒስትሮች ኮሚሽንም ወደ ከፍተኛ የጋራ ኮሚሽን አድጓል፡፡

ባለፉት ዓስር ዓመታት እየጎለበተ በመጣው የኢትዮጵያ እና ኬኒያ ግንኙነት ሁለቱ ሀገራት በመካከላቸው ያለውን የወዳጅነት ትብብርና የኢኮኖሚ ግንኙነት ወደ ላቀ ደረጃ ለማሳደግ የሚያስችል የልዩ ኢኮኖሚ መብት ተጠቃሚነት የትብብር ስምምነት (Special Status Agreement -SSA) በ2012 ዓ.ም ተፈርሟል፡፡ በሁለቱ አገራት መካከል የኤሌክትሪክ ሀይል አቅርቦት ስምምነት እ.ኤ.አ በ2011 የተፈረመ ሲሆን ኢትዮጵያ ኬኒያ የሚደርስ የከፍተኛ ኃይል መስመር ግንባታ እያከናወነች ነው። በተጨማሪ

አገራቱ የጋራ ድንበራቸውን የልማት ቀጠና ለማድረግ የሚያስችላቸው ፕሮጀክት ላይ በመስማማት እየተገበሩ ነው፡፡ አገራችንን ከኬንያ ጋር በባቡር መስመር ለማገናኘት በ2012 በተደረሰው ስምምነት መሰረትም የአዋጪነት ጥናትና የፕሮጀቶች ጽ/ቤቶችን የማቋቋም ስራ ተጀምሯል። በመንገድ ግንባታ ዘርፍም ከናይሮቢ አዲስ አበባ ያለው ወደ 1000 ኪ.ሜ በግንባታ ላይ ነው። በንግድ መስክ ንግድ እና የሰዎችን ዝውውር ለማሳለጥ የሚያስችል የአንድ ፍተሻ የጋራ ጣቢያ One- stop border post በመገንባት ላይ ይገኛሉ።

ኢትዮጵያና ሱዳን በተለያዩ ጊዜያቶች ሲሞቅና ሲቀዘቅዝ ከነበረ ግንኙነት ወጥተው ግንኙነታቸውን በሁሉም መስክ በማጠናከር ወደ ኢኮኖሚያዊ ውህደት በማምራት ላይ ይገኛሉ። ባለፉት አሥር ዓመታት ሱዳን ከራሷ ጥቅም በመነሳት በታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ዙሪያ ድጋፏን እንድትሰጥ ከፍተኛ ዲፕሎማሲያዊ ስራዎች የተከናወኑበት ነው፡፡ ንግድ እና ኢንቨስትመንትን አስመልክቶ የሱዳን ባለጸጋዎች በበርካታ ዘርፎች ተሰማርተዋል። በሁለቱ ሀገራት መካከል በኢኮኖሚው መስክ የተፈረሙ ስምምነቶችን ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ለማድረግ እንዲቻል የተለያዩ የኢኮኖሚ ዘርፍ መ/ቤቶች ተሳታፊ የሆኑባቸው ኮሚቴዎች ተዋቅረው ውጤታማ ስራዎችን እያከናወኑ ነው። በተጨማሪ በጠረፍ ንግድ፣ በባንኪንግና በጉምሩክ ዘርፎች ስምምነቶች መፈረማቸውና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በካርቱም ቅርንጫፍ መክፈቱ ተጠቃሽ ስኬቶች ናቸው። በትራንስፖርት መሠረተ-ልማት ዘርፍ ከአዲስ አበባ ካርቱም የመንገደኞች ማጓጓዣ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል ስምምነት የተፈረመ ሲሆን የባቡር መንገድ ለመገንባት ስራዎች ተጀምረዋል፡፡

አገራችን አሸባሪውን አልሸባብን በመዋጋት ሶማሊያ ከሽብር ሃይሉ ነጻ እንድትወጣ እና ማእከላዊ መንግስቷ እንዲጠናከር ቀዳሚ ሚና ተጫውታለች፡፡ በኢጋድ አባል አገርነቷም እ.ኤ.አ. ከ2004 ጀምሮ የሶማሊያ ፌዴራል መንግስት እንዲቋቋም እና አለም አቀፍ ድጋፍ እንዲያገኝ ከፍተኛ የዲፕሎማሲ ስራ ተከናውኗል፡፡ በተጨማሪ በፌደራል የመንግስት አስተዳደር ዙሪያ የራሷን ልምድ በማካፈል፣ ትምህርት እና ስልጠናዎችን በመስጠት እና የሶማሊያ ፌዴሬሽን አባል ክልሎች በተለያዩ ጉዳዮች ላይ እንዲስማሙ በማድረግ ድጋፏን ሰጥታለች፡፡ በ2011 በሀገራችን ሠራዊትና በአፍሪካ

ህብረት የሶማሊያ ሰላም አስከባሪ ልዑክ ድጋፍ አልሻባብ ከሞቃዲሾና ከተለያዩ ከተሞች ለቆ ከወጣ ወዲህ ሶማሊያ አንጻራዊ ሰላም ያለባት ሀገር በመሆኗ ከ2012 ጀምሮ በፓርላማና ፕሬዚዳንት የምትመራ ሀገር መሆን ችላለች። ከአገሪቱ ጋር በወታደራዊ ትብብር፣ በፖሊሳዊ ትብብር፣ በትምህርት፣ በሲቪል አቪዬሽንና በኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን በኩል የሁለትዮሽ ስምምነቶችን የተፈረመ ሲሆን በትምህርት ዘርፍ ከ500 በላይ የስኮላርሽፕ እድል ለሶማሊያ ወጣቶች ተሰጥቷል።

እ.ኤ.አ. በሐምሌ 2011 ደቡብ ሱዳን ሉዓላዊት ሀገር ሆና ከተፈጠረችበት ጊዜ ጀምሮ አገሪቱ ዘላቂ ሰላምና ልማት የሚካሄድባት ጎረቤት አገር እንድትሆን የበኩላችንን ተከታታይ ጥረት እያደረግን እንገኛለን። በተለይ ከነጻነት ማግስት ጀምሮ አገራችን በሁለቱ ሱዳኖች መካከል እልባት ያላገኙ አከራካሪ ጉዳዮች በስምምነት እንዲቋጩ ከፍተኛ ጥረት አድርጋለች። ሁለቱም አገራት በአቢዬ ግዛት የሚሰፍረው የሰላም አስከባሪ ሃይል ከኢትዮጵያ እንዲመጣ መወሰናቸው የዚህ ውጤታማ ዲፕሎማሲያዊ ስራ መገለጫ ነው፡፡ በደቡብ ሱዳን ያለውን የእርስ በርስ ግጭት በሚመለከት ከዲሴምበር 15/2013 ተጀምሮ የብዙሃንን ህይወት የቀጠፈው እና ለስደት የዳረገው ግጭት እንዲፈታ በተደረገው ጥረት በምስራቅ አፍሪካ በይነ መንግስታት ድርጅት በተቋቋመው አሸማጋይ ኮሚቴ አማካኝነት ድርድሮች እንዲደረጉ በመደገፍ እ.ኤ.አ ኦገስት 2015 የሰላም ስምምነቱ እንዲፈረም ተደርጓል። ከዚሁ ጎን ለጎን የደ/ሱዳን መንግሥት ተቋማዊ አቅም እንዲገነባ ኢትዮጵያውያን ባለሙያዎችን ወደ ጁባ በመላክ እና ደ/ሱዳናውያን ወደ ኢትዮጵያ መጥተው በተለያዩ የመንግስት አስተዳደር ሙያዎች ሥልጠና እንዲያገኙ ተደርጓል። በተጨማሪ ደቡብ ሱዳንን በመሰረተ ልማት ግንባታ ለማገዝ የሚያስችሉ ስምምነቶች ተፈርመዋል፡፡

አገራችን ከኤርትራ መንግስት ጋር ያለው አለመግባባት ተፈቶ ወደሰላማዊ ጉርብትና ለመግባት የኖረ ቁርጠኝነቷን ስታሳይ ቆይታለች፡፡ የኤርትራ መንግስት በኢትዮጵያ ለቀረበለት የሰላም ድርድር አዎንታዊ ምላሽ የሌለው በመሆኑ የድንበር ማካለሉም ሆነ ግንኙነቱን የማሻሻል ጥረት ስኬታማ አልሆነም። የኤርትራ መንግስት የሽብር ድርጅቶችን በመደገፍ የአገራችንን እንዲሁም የክፍለ አህጉሩን ሰላም ለማደፍረስ የሚያደርገውን ጥረት ለማስቀም

አለም አቀፍ ሕግን መሰረት በማድረግ በተ.መ.ድ እንዲሁም በአፍሪካ ህብረት ማእቀቦች እንዲጣሉበት ያስቻለ የዲፕሎማሲ ስራ ተከናውኗል፡፡ የኤርትራ መንግስት ለአገራችን እና ለክልሉ ሰላም ጎጂ ተግባራትን ከማከናወን ያልተቆጠበ ቢሆንም ከአገራቸው በመሸሽ ወደኢትዮጵያ የሚገቡትን አያሌ ቁጥር ያላቸው ኤርትራዊያን በመቀበል እና ጥገኝነት በመስጠት የሚያስመሰግን ተግባር እያከናወንን እንገኛለን፡፡

## አካባቢያዊ የኢኮኖሚ ውህደትን በተመለከተ፥

አገራችን ለአካባቢያዊ የኢኮኖሚ ውህደት ከፍ ያለ ግምት የምትሰጥ በመሆኑ በኢጋድ ውስጥ ንቁ ተሳትፎ ታደርጋለች፣ የLamu Port-South Sudan-Ethiopia Transport (LAPSSET) ፈርማለች እንዲሁም እ. ኤ. አ በ2015 የኖርዘርን ኮሪዶር ኢንተግሬሽን ፕሮጀክት አባል በመሆን ከ16ቱ የኮሪደሩ ፕሮጀክቶች መካከል በሁለቱ ማለትም በሃይል ማመንጨት እና ትስስር እንዲሁም በባቡር መሠረተ-ልማት ለመሳተፍ ወስናለች፡፡

## የምስራቅ አፍሪካ በይነ መንግስታት ድርጅት (ኢጋድ)

ባለፉት አሥር ዓመታት ኢጋድ የተቋቋመበትን ዓላማ ለማሳካት አብይ ተግባራትን አከናውኗል፡፡ እነዚህም ደቡብ ሱዳን ሪፐብሊክ የራሷን ዕድል በሰላማዊ መንገድ እንድትወስን ማስቻሉ፣ በሶማሊያ የሽግግር መንግስት ብሎም የፌዴራል መንግስት እንዲመሠረት ማስቻሉ፣ የኤርትራ መንግስት በአካባቢውና በኢጋድ አባል ሀገራት በሚያደርገው የጠብ አጫሪነት ትንኮሳ ሳቢያ በአፍሪካ ህብረት ብሎም በተመድ ማዕቀብ እንዲጣልበት ማድረጉና በደቡብ ሱዳን መንግስትና ተቀናቃኝ ፓርቲዎች መካከል የሠላም ስምምነት እንዲፈረም ማስቻሉ ይጠቀሳሉ። ኢጋድ Minimum Integration Plan አዘጋጅቶ በአባል ሀገራቱ ዘንድ ኢኮኖሚያዊ ውህደት ለማምጣት መሠረት መጣሉም ሌላው ስኬቱ ነው። አገራችንም ከላይ ለተጠቀሱት የኢጋድ ስኬቶች መሳካት ጉልህ ሚና ተጫውታለች።

በኢጋድ አባል አገራት መካከል የኢኮኖሚ ትስስር ለመፍጠር የሚያስችል አደረጃጀት ለመቀየስ ስራዎች እየተከናወኑ ነው፡፡ ከኢጋድ አባል አገራት መካከል የኢትዮጵያ፣ የጅቡቲ፣ የሶማሊያና የሱዳን መሪዎች በ2008 ዓ.ም አራቱን አገራትና ወደፊትም ኤርትራን ታሳቢ የሚያደርግ አንድ የአፍሪካ

ቀንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ (Horn of Africa Economic Community) ስለሚመሰረትበት ሁኔታ ጥናት እንዲደረግ በወሰነው መሰረት ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሀላፊነቱን ወስዶ የመጀመሪያ ደረጃ የጥናት ሰነድ አዘጋጅቶ አቅርቧል።

### 1.1.2. ኢትዮጵያ ከሌሎች አፍሪካ አገሮች ጋር ያላት ግንኙነት

አገራችን በአምስቱም የአፍሪካ ክልሎች ካሉ አገራት ጋር ያላት ሁለንተናዊ ግንኙነት የአገራቱን የጋራ ጥቅም ለማስከበር ያለመ እና የኢኮኖሚ ትስስሩን በማጠናከር የአፍሪካ ህብረትን እንዲሁም የአፍሪካ ለልማት አዲስ አጋርነት (NEPAD) ግቦችን ለማሳካት ያለመ ነው፡፡ በዚህም መሰረት ባለፉት 10 አመታት ብቻ በተለያዩ ዘርፎች ከአፍሪካ አገራት ጋር 344 ስምምነቶች ተፈርመዋል፡፡ እነዚህ ስምምነቶች ንግድ፣ ግብርና፣ ትምህርት፣ ጤና፣ ኢንደስትሪ፣ የታዳሽ ሃይል ልማት፣ ሰላም እና ጸጥታ እና የመሳሰሉ ዘርፎች ላይ ያተኮሩ ናቸው፡፡

ከአፍሪካ ወዳጅ አገራት ጋር ያለው መልካም ግንኙነት በባለብዙ መድረኮች ላይም የሚንጸባረቅ ሲሆን በአፍሪካ ህብረት የድርጅቱን መርሆዎች ለማስፈጸም እና የህብረቱን የልማት፣ ሰላም እና ጸጥታ እንዲሁም ሌሎች አጀንዳዎች ለመተግበር አመቺ ሁኔታ ፈጥሯል ፡፡ በተጨማሪም በተባበሩት መንግስታት ድርጅት እና ሌሎች አለም አቀፍ ተቋማት የአፍሪካ ቡድኖች ተቋቁመው እርስ በርስ በመደጋገፍ እና የአህጉሪቱ ጥቅም እንዲጠበቅ ስራዎች ሲከናወኑ ቆይተዋል አገራችንም በአፍሪካ ቡድኖች ንቁ ተሳትፎ ታደርጋለች፡፡ በዚህም አገራችን የአፍሪካ ህብረት የተ.መ.ድ የጸጥታው ምክር ቤት አባልነት ብቸኛ እጩ ሆና በመቅረብ የምክር ቤቱ አባል አገር ሆና ተመርጣለች፡፡

### 1.1.3. ሰላም እና ደህንነት

ባለፉት አስር አመታት የአገራችንን እንዲሁም የክፍለ አህጉሩን ሰላም እና ደህንነት በማስከበር ረገድ ስራዎች ተከናውነዋል፡፡ በኢጋድ አማካኝነት የድንበር ዘለል ወንጀሎች የሆኑትን የሽብር ወንጀል፣ ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር፣ የጦር መሳሪያ ንግድ እና ዝውውር፣ የዝሆን ጥርስ ንግድ እና ዝውውር፣ የአደገኛ እጽ ንግድ እና ዝውውርን ለመግታት ጥረቶች

ተደርገዋል፡፡ በፍትህ ዘርፍ ትብብር ለመመስረት ሲባልም በኢ.ጋድ አገራት መካከል የፍትህ ዘርፍ ትብብር ስምምነት የተፈረመ ሲሆን በተናጠል ከጅቡቲ እና ሱዳን ጋር ወንጀለኞችን አሳልፎ የመስጠት ስምምነት ተፈርሟል፡፡ በተጨማሪ በምስራቅ አፍሪካ ያለውን ሁኔታ ከግምት ያስገባ የጸረ ሽብር ተግባራትን በማከናወን ከአሜሪካ፣ አውሮፓ እና ሌሎች አገራት ጋር በመተባበር እነዚህ ወንጀሎች የአገራችን እንዲሁም የክልሉ የደህንነት ስጋት መሆናቸው እንዲቀር የተለያዩ ተግባራት እየተከናወነ ይገኛል፡፡

አገራችን የሰላም አስከባሪ ሃይል በማሰማራት ከአፍሪካ ቀደምት እንዲሁም በአለም ሁለተኛ ደረጃ ላይ ትገኛለች፡፡ የአገራችን የሰላም አስከባሪ ሃይሎች ስራቸውን በውጤታማነት እንዲያከናውኑ እና አገራችን በዘርፉ ያደረገችው አስተዋጽኦ እውቅና እንዲሰጠው የተለያዩ ዲፕሎማሲያዊ ጥረቶች ተደርገዋል፡፡ አገራችን የተ.መ.ድ የሰላም ማስከበር ተልዕኮን ከማጠናከር ጋር በተያያዘ ክልላዊ ኮንፈረንስ ያስተናገደች ሲሆን ለኮንፈረንሱ ስኬታማነት አስፈላጊው ድጋፍ ተደርጓል። በተጨማሪ አገራችን በአፍሪካ ህብረት በኩል በቡሩንዲ፣ ሊቢያ፣ የሴንትራል አፍሪካ ሪፐብሊክ፣ ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጎ ያሉት የሰላም እና ደህንነት መደፍረሶች እንዲቆሙ የአገራቱን ሉአላዊነት ባከበረ እና በውስጥ ጉዳያቸው ጣልቃ መግባት በማያስከትል መልኩ ዲፕሎማሲዊ ጥረት አድርጋለች፡፡

## 1.1.4. የድንበር ተሻጋሪ ሃብቶች

አገራችን ከቅርብ እና ከሩቅ ጎረቤቶቿ ጋር እንድትተሳሰር ያደረጉ ወንዞች ባለቤት ስትሆን የተፋሰስ ሀገራት በእኩልነት እና በፍትሐዊነት የወንዞቹ ተጠቃሚ የሚሆኑበትን ስርዓት መዘርጋት እንዳለበት ጽኑ አቋም አላት። አገራችን ከእነዚህ ወንዞች ተጠቃሚነቷን ለማረጋገጥ ሁለት አብይ አካሄዶችን ተከትላለች። አንደኛው ግዙፍ የውሃ ልማት ስራዎችን በብሔራዊ ደረጃ ማከናወን ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ከተፋሰሱ ሀገራት ጋር ትብብርን ማጠናከር ናቸው። በመሆኑም በእነዚህ አስር ዓመታት ውስጥ አራት የኤሌክትሪክ ሃይል ማመንጫ ግድቦችን አስመርቃለች። በገናሌ ወንዝ ላይ የሚገነባው የገናሌ 3 ኃይል ማመንጫ ግድብ የተጀመረውም በ2004 ዓ.ም ነው። ከዚሁ ባሻገር በአባይ ወንዝ ላይ የሚገነባው ግዙፉ የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ

የተጀመረው እና ከ60 በመቶ በላይ የተጠናቀቀውም በእነዚህ 10 ዓመታት ነው።

ከድንበር ተሻጋሪ ወንዞች ተፋሰስ አገራት ጋር ያለውን ግንኙነት በሚመለከት 13 ዓመታት ከፈጀ ድርድር በኋላ በግንቦት 2002 ዓ.ም የናይል የትብብር ማዕቀፍ ስምምነት (Agreement on the Cooperative Framework of the Nile-CFA) ተፈርሟል። ይህ ስምምነት ከጫፍ እንዲደርስ ከሌሎች የአባይ ወንዝ የላይኛው ተፋሰስ ሀገራት ጋር በመሆን አገራችን አይተኬ የመሪነት ሚና ተጫውታለች። ስምምነቱን በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያን ጨምሮ ሩዋንዳ፣ ታንዛኒያ፣ ዩጋንዳ፣ ኬንያ እና ቡሩንዲ የፈረሙት ሲሆን ኢትዮጵያ፣ ሩዋንዳ እና ታንዛኒያ ደግሞ አጽድቀውታል። ቀሪዎቹ ሀገራትም በማጽደቅ ሂደት ላይ ሲሆኑ ደቡብ ሱዳን ወደስምምነቱ ለመግባት (acession) ሂደት ላይ ናት።

የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ መጀመርን ተከትሎ በአባይ ወንዝ አጠቃቀም ዙሪያ ለወትሮው ከግብጽ ጋር አንድ ዓይነት አቋም ታራምድ የነበረው ሱዳን ለግድቡ ያላትን ድጋፍ በከፍተኛ አመራር ደረጃ ገልጻለች። ከግብጽ ጋርም ቢሆን ጉዳዩ ላይ በዲፕሎማሲያዊ መንገድ ፣ በግልጽነት እና ወንድማማችነት መንፈስ ለመስራት አገራችን ቁርጠኝነቷን አሳይታለች። የዚህ ውጤት የሆነውም በመጋቢት 2007 ዓ.ም. በካርቱም በሶስቱ ሀገሮች መሪዎች የተፈረመው "የህዳሴ ግድብ የመርሆዎች መግለጫ ስምምነት/Agreement on the Declaration of Principles (DoP)" ተጠቃሽ ስኬት ነው።

ከጊቤ ግድቦች ጋር በተገናኘ በተለያዩ መድረኮች የሚቀርቡብንን ክሶችም እየተወጣን የመጣነው በእነዚህ አስር ዓመታት ውስጥ ነው። በተለይ በተባበሩት መንግስታት የትምህርት፣ የሳይንስ እና የባህል ድርጅት (UNESCO) ጊቤ 3 ግድብን አስመልክቶ የቀረበው ክስ የግድብ ግንባታ ሂደታችንን እንዳያደናቅፍ ማድረግ የተቻለው ባለፉት አስር ዓመታት ውስጥ ነው።

## 1.2.የሰሜን እና ደቡብ አሜሪካ አገራት

በሰሜን እና ደቡብ አሜሪካ ካሉ አገራት ጋር ያለን ግንኙነት በመርህ ላይ በመመስረት የጋራ ጥቅምን ማሳካትን ኢላማ ያደረገ ሲሆን ባለፉት አስር

አመታት ከነባሮቹ በተጨማሪ ከአዳዲስ አገራት ጋር አጋርነት የተፈጠረ ሲሆን 23 ስምምነቶችም ተፈርመዋል፡፡

ባለፉት አስር ዓመታት በአካባቢያችን ሰላምን በማስጠበቅና ሽብርተኝነትን በመዋጋት ረገድ ከአሜሪካ ጋር ጠንካራ ግንኙነት ተፈጥሯል፡፡ ፕሬዝዳንት ባራክ ኦባማን ጨምሮ የተለያዩ የአሜሪካ ባለስልጣናት እና የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት አባላትም በአገራችን ጉብኝት አድርገዋል፡፡ በተጨማሪም የአሜሪካ እና የአገራችን መንግስት የትብብር ዘርፎችን የሚገመግሙባቸው ቋሚ የምክክር መድረኮች ተዘጋጅተዋል፡፡

በተመሳሳይ ከካናዳ ጋር ያለው ግንኙነት እየተጣናከረ መጥቶ የኢትዮ-ካናዳ ምክክር መድረክ ተቋቁሞ አምስት ስብሰባዎችን አካሂዷል። ከኩባ፣ ሜክሲኮ፣ እና ብራዚል ጋር ያለው ግንኙነት እያደገ የመጣ ሲሆን ከኩባ ጋር የጋራ ሚኒስትሮች ጉባኤ ለመመስረት የሚያስችል ስምምነት ተፈርሟል፡፡ በተጨማሪም በአፍሪካ - ደቡብ አሜሪካ አገራት መድረክ እንዲሁም በሁለተኛው የአፍሪካ ህብረት - የአሜሪካ አገራት ድርጅት ጉባኤ ላይ ተሳትፎ ተደርጓል፡፡

## 1.3. የአውሮፓ ህብረት እና የአውሮፓ አገራት

አውሮፓ የኒዮሊበራል አስተሳሰብ መሰረት ከመሆኑም ባሻገር አገራችንን ጨምሮ ሌሎች አገራት ርዕዮተ ዓለሙን እንዲከተሉ ከፍተኛ ጫና በማድረግ ላይ በነበሩበት ወቅት አገራችን የተለየ ልማታዊ ፖሊሲ በመቅረጿ ምክንያት ጫናዎች ሲፈጠሩባት ቆይታለች። ይሁን እንጂ ይህንን የምዕራባውያን ጫና በመቋቋምና ለአገራችን ይጠቅማል የተባለውን የልማታዊ መንግስት ፖሊሲ እነዚህ አካላት እንዲረዱ በማድረግ የፖሊሲ ልዩነት እንዳለ ሆኖ ግንኙነታችንን የሚያጠናክር ሰፊ ዲፕሎማሲያዊ ስራዎች ተከናውነዋል። የአገራችን የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ለእስያ አገራት ወገናዊነት ያሳያል በሚል የተሳሳተ አመለካከት ለነበራቸው የአውሮፓ አገራት ፖሊሲዎቻችን ከአገራችን የልማትና ዕድገት ፍላጎት የመነጨ መሆኑን በማስገንዘብ ሚዛናዊ (balanced) የሆነ ግንኙነት ለመመስረት በቅተናል።

ከዚህ በተጨማሪ ከአውሮፓ ህብረት እና ከአገራቱ ጋር የነበረንን ግንኙነት በሰብአዊ መብት፣ ዲሞክራሲና እርዳታ ላይ የታጠረ ሲሆን ባለፉት 10 ዓመታት በተሰሩ ስራዎች ግንኙነታችንን ሰፋት ያለውና ከእርዳታ ይልቅ

በኢንቨስትመንት፣ በሥራ ፈጠራ፣ በቴክኖሎጂና በሰላምና ጸጥታ ላይ እንዲያተኩር ማድረግ ተችሏል። በመሆኑም በአሁኑ ወቅት የአውሮፓ ህብረት እና የአውሮፓ አገራት የአገራችን ቁልፍ የልማት አጋሮች ናቸው፡፡ ከአውሮፓ ህብረት፣ እንግሊዝ፣ ጀርመን፣ ቱርክ፣ ጣልያን፣ ፈረንሳይ፣ ኔዘርላንድ ጋር ስትራቴጂክ አጋርነትን መመስረትና ማጠናከር ተችሏል። ባለፉት 10 ዓመታት ብዛት ያላቸው የአውሮፓ መሪዎች በአገራችን ጉብኝት ሲያደርጉ በተመሳሳይ የአገራችን መሪዎች በተለያዩ ጊዜያት ጉብኝት አድርገዋል። ከአውሮፓ አገራት ጋር የፖለቲካ ምክክር የሚካሄድበት የጋራ መድረክ ተመስርቶ ተጠቃሚነታችንን ያሳደጉ ውይይቶች የተደረገ ሲሆን ከተለያዩ የአውሮፓ አገራት ጋር 58 ስምምነቶችም ተፈርመዋል፡፡

ከአውሮፓ ህብረት ጋር ያለን ግንኙነት እየተጠናከረ የመጣ ሲሆን የግንኙነቱ አርባ አመት ተዘክሯል፡፡ የአውሮፓ ህብረት ለኢትዮጵያ ትልቁና ዋነኛው ስትራቴጂክ አጋር ሲሆን፣ ህብረቱ በኮቶኑ ስምምነት መሠረት የሚያካሂደው የልማት ትብብር በየጊዜው እያደገ የመጣና ለአገራችንም ልማት አስተዋጽኦ እያበረከተ የሚገኝ ነው፡፡ አገራችን በ European Development Fund[EDF] ከ 1 ቢሊዮን ዩሮ በላይ የልማት ትብብር ተጠቃሚ ሆናለች፡፡ በፖለቲካ እና በፀጥታ ጉዳዮች ዙሪያም በተለይ ከአፍሪካ ቀንድ ሰላምና ፀጥታ ጋር በተያያዘ ከፍተኛ ትብብር እና ድጋፍ በመደረግ ላይ ይገኛል፡፡ ከአውሮፓ ህብረት ተቋማት ጋር ስፋት ያላቸው የፖለቲካ የምክክር መድረኮች የተካሄዱ ሲሆን ግንኙነቱን ወደ ላቀ ደረጃ ለማሸጋገር የሚያስችል strategic engagement ሰነድ ተፈርሟል፡፡ ይህ ሰነድ አገራችን እና ህብረቱ በልማት፣ ሰላም እና ጸጥታ፣ በዴሞክራሲ እና ሰብአዊ መብቶች መከበር እንዲሁም በሌሎች ዘርፎች የሚያደርጉት ትብብር ዘላቂ እና የረዥም ጊዜ ትልሞችን ማሳካት ኢላማ ያደረገ እንዲሆን ያስችላል፡፡

በህብረቱ በኩል ከሚደረገው ትብብር በተጨማሪ ከፈረንሳይ፣ እንግሊዝ፣ ጀርመን፣ ጣልያን፣ ስፔን፣ ዴንማርክ፣ ስዊድን፣ ኔዘርላንድ እና ሌሎች የህብረቱ አባል አገራት ጋር ያለው ሁለንተናዊ ግንኙነት እንዲጠናከር የተለያዩ ስራዎች ተከናውነዋል፡፡ የጀርመን መንግስት ይፋ ባደረገው Marshal Plan with Africa እና G20 compact with Africa አገራችን ቀዳሚ

ተጠቃሚ እንድትሆን ዲፕሎማሲያዊ ስራዎች እየተከናወኑ ይገኛል፡፡ ከጀርመን ጋር ኢ.ኤ.አ ከ1964 ዓ.ም ጀምሮ ቋሚ የልማት ትብብር ማዕቀፍ ባለፉት 10 ዓመታት 334 ሚሊዮን የልማት ፋይናንስ ድጋፍ ተገኝቷል። ከዚህ በተጨማሪ ጀርመን ለአገራችን የአቅም ግንባታ፣ ቴክኒክና ሞያ ትምህርት፣ በግብርና፣ በተፈጥሮ ሀብትና ብዝሀ ሕይወት ጥበቃ ዘርፎች ጠንካራ ድጋፍ ታደርጋለች።

ከእንግሊዝ ጋር ያለው ግንኙነት ታሪካዊ ከመሆኑም በተጨማሪ በተጨባጭ ጉዳዮች ላይ ያተኮረ እና ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጠው ነው፡፡ እንግሊዝ የአገራችን ዋነኛ የልማት አጋር ስትሆን በየዓመቱ ለአገራችን 300 ሚሊዮን ፓውንድ የሚደርስ ገንዘብ በድጋፍ እየሰጠች ትገኛለች። እንግሊዝ የተ.መ.ድ የፀጥታው ምክር ቤት ቋሚ አባል እንደመሆኗ መጠን በም/ቤቱ በአፍሪካ የሰላምና የፀጥታ ጉዳዮች ዙሪያ በሚደረጉ ውይይቶች ላይ ከኢትዮጵያ ጋር በመተባበርና በመመካከር እየሰራች ትገኛለች፡፡ የእንግሊዝ ባለሥልጣናት በተለያዩ ጊዜያት በሀገራችን ጉብኝት በማድረግ በሽብርተኝነት፣ በልማት ትብብር እና ተዛማጅ ጉዳዮች ዙሪያ ምክክሮችን ያካሂዳሉ፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ዓለምአቀፍ ዕውቅና ያላቸው የእንግሊዝ ኩባንያዎች በሀገራችን ኢንቨስት የማድረግ እንቅስቃሴ ጀመረዋል። ይህ ግንኙነት እንዲጎለብት ጠንካራ የዲፕሎማሲ ስራዎች ተከናውነዋል፡፡

ኢ.ኤ.አ. ከ2005 ጀምሮ ከቱርክ ጋር ያለው ግንኙነት እየተጠናከረ መጥቶ የቱርክ ባለሃብቶች በአገራችን ያላቸው ኢንቨስትመንት በካፒታል መጠን ሲታይ በመጀመሪያ ደረጃ ላይ የሚገኝ ሲሆን በ2020 በአገራቱ መካከል ያለውን የንግድ ልውውጥ አንድ ቢሊየን ዶላር ለማድረስ እየተሰራ ነው፡፡ በሌላ በኩል ከቱርክ ጋር በየዓመቱ የፖለቲካ ምክክር መድረክ እየተካሄደ ሲሆን አገራችን በአፍሪካ- ቱርክ ጉባኤ ላይም ንቁ ተሳትፎ አድርጋለች፡፡

ከአገራችን ጋር ከመቶ ዓመታት በላይ ያስቆጠረ ግንኙነት ያላት ፈረንሳይ በአፍሪካ ቀንድ ሰላም እንዲሰፍን የምናደርገውን እንቅስቃሴን ጨምሮ በተ.መ.ድ የጸጥታው ም/ቤት በኩል አስፈላጊውን ድጋፍ ታደርጋለች። ኢ.ኤ.አ ከ2011-2014 ፈረንሳይ የ337 ሚሊዮን ዩሮ የልማት ትብብር ድጋፍ ያደረገች ሲሆን ትላልቅ የፈረንሳይ ኩባንያዎች በአገራችን በሚካሄዱ የመሰረተ ልማት ፕሮጀክቶች ላይ በአማካሪነት ይሳተፋሉ፡፡

ሩሲያ የተ.መ.ድ የፀጥታ ጥበቃው ምክር ቤት ቋሚ አባል እንደመሆኗ መጠን በዚያ መድረክ ላይ አፍሪካና ብሎም ኢትዮጵያን በሚመለከቱ ጉዳዮች ዙሪያ ስትደግፈን ቆይታለች፡፡ የኢትዮጵያ እና ሩሲያ የጋራ ኮሚሽን ተመስርቶ ጉባኤዎችን ያካሄደ ሲሆን ባለፉት አስር አመታት ከሩሲያ ጋር ዘጠኝ ስምምነቶች ተፈርመዋል፡፡ የጋራ ኮሚሽኑ የተፈረሙ ስምምነቶችን አፈጻጸም በመገምገም በተለያዩ የትብብር መስኮች የአገራቱ ግንኙነት ስለሚጠናከርበት ሁኔታ አቅጣጫ አስቀምጧል፡፡ በተለያዩ ጊዜያት በመሪዎች ደረጃ ጉብኝት በማካሄድ ከሩሲያ ጋር ያለንን ግንኙነት ለማጠናከር እየተሰራ ሲሆን በዚህም በሰላማዊ ኒኩሌር ሀይል በትብብር ለመስራት ብሎም ከፍተኛ የቴክኖሎጂ ሽግግር ለማድረግ የሚያስችል መነሻ ስምምነት ተፈርሟል።

ከስዊዲን፣ ሰዊዘርላንድ፣ ኖርዌይ፣ ጋር በተለያዩ ዘርፎች ያሉ ግንኙነቶች እዲጠናከሩ ጥረቶች ተደርገዋል፡፡ ኖርዌይ በኢኮኖሚ እና ልማት ትብብር መስክ በአሁኑ ሰዓት የኢትዮጵያ የልማት አጋር ከሆኑት 6 አገሮች መካከል አንዷ ስትሆን በአረንጓዴ ልማት መስክ አና በሰላም እና ጸጥታ ዘርፍ ግንኙነቶችን ለማጠናከር ስራዎች እየተከናወኑ ነው፡፡ አየርላንድ፣ ዴንማርክ፣ ስዊድን፣ ኖርዌይ አገራችን ላይ ተኮረ ስትራቴጂ በመንደፍ የአገራችን የልማት ጉዞ ለመደገፍ እየሰሩ ይገኛሉ።

## 1.4.የመካከለኛው ምስራቅ አገራት

ባለፉት አስር አመታት ከመካከለኛው ምስራቅ አገራት ጋር ያለውን ወዳጅነት ለማጠናከር የተለያዩ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡ በአገራችን ያለውን የኢንቨስትመንት እድል የበለጠ በማስተዋወቅ በነዳጅ ሃብት የበለጸጉት የክፍለ አለሙ አገራት እና ዜጎቻቸው በአገራችን መዋዕለ ነዋያቸውን እንዲያፈሱ ለማድረግ ተችሏል ፡፡ በዚህም ከኳታር፣ ከኩዌት፣ ሳዑዲ አረቢያ፣ የተባበሩት አረብ ኤምሬቶች እና የመን ጋር ያለው ትብብር እየተጠናከረ ይገኛል ፡፡ ግንኙነቱን የበለጠ ለማጠናከርም ከሳዑዲ አረቢያ፣ የተባበሩት አረብ ኤምሬቶች እና ኳታር ጋር የጋራ ሚኒስትሮች ጉባኤዎች ተመስርተዋል፡፡

ባለፉት አስር አመታት 46 ሰምምነቶች ከመካከለኛው ምስራቅ አገራት ጋር የተፈረሙ ሲሆን፡፡ ስምምነቶቹ በአየር አገልግሎት፣ ግብርና፣ ትምህርት ፣ የእንስሳት እና አሳ ሃብት ልማት እና ንግድ ላይ ያተኮሩ ናቸው፡፡ ከመካከለኛው ምስራቅ አገሮች ጋር ባለው ግንኙነት ሌላው ትኩረት

የሚደረግበት መስክ ወደ አገራቱ ለስራ የሚጓዙ ኢትዮጵያውያን መብት እና ደህንነት ሲሆን ሕገወጥ ጉዞዎችን ለመግታት እና የሰራተኞችን መብት ለማስጠበቅ የሚያስችሉ የስራ ስምሪት ስምምነቶች ከሳዑዲ አረቢያ እና ከተባበሩት አረብ ኤምሬቶች ጋር የተፈረመ ሲሆን ከሊባኖስ ጋር ድርድር እየተከናወነ ይገኛል፡፡

ሌላው በክፍለ አለሙ የምትገኝ አገር እስራኤል ስትሆን ባለፉት አስር አመታት አገሪቱ ከአገራችን ጋር ያላትን ግንኙነት ከማስቀጠል በተጨማሪ ከአፍሪካ ሃገራት ጋር ያላትን ትብብር ለማጠናከር ባደረገችው ጥረት ድጋፍ ተደርጎላታል፡፡ ባለፉት አስር አመታት በአገራችን እንዲሁም በእስራኤል ከፍተኛ የስራ ሃላፊዎች ጉብኝቶች በሁለቱም አገራት የተከናወኑ ሲሆን ከመንግስት ለመንግስት ግንኙነቶች በተጨማሪ የህዝብ ለህዝብ ግንኙነቱ እንዲጠናከር ለማስቻል ቤተ እስራኤላዊያን የትውልደ ኢትዮጵያዊነት እውቅናን እንዲያገኙ የሚያስችላቸው ስርአት ተዘርግቷል፡፡ የእስራኤል ባለሃብቶች እና ነጋዴዎችም በአገራችን መዋዕለ ነዋያቸውን የሚያፈሱበት ሁኔታ እንዲመቻች የተለያዩ ስራዎች ተከናውነዋል፡፡

## 1.5. የኤስያ አገራት

አገራችን ከድህነት ለመውጣት በምታደርገው ጉዞ ከኤስያ አገራት የምትቀስማቸው ልምዶች አሉ፡፡ በዚህም ቻይና፣ ጃፓን፣ ህንድ፣ ደቡብ ኮሪያን ከመሳሰሉ አገራት ጋር ያለው ትብብር እየተጠናከረ መጥቷል፡፡ ባለፉት አስር አመታት በተለያዩ የትብብር መስኮች 77 ስምምነቶች ከእስያ እና ኦሽኒያ አገራት ጋር ተፈርመዋል፡፡

በአስር አመቱ የጃፓን እና የደቡብ ኮሪያ መሪዎች በአገራችን ጉብኝት ያደረጉ ሲሆን ከስሪ ላንካ፣ ከባንግላዴሽ፣ ከኢንዶኔዥያ፣ ከፊሊፒንስ እና ከታይላንድ ጋር ያሉትን ግንኙነቶች ለማጠናከር በተለያዩ ደረጃዎች ውይይቶች ተደርገዋል፡፡

ከህንድ ጋር ያለው የፖለቲካ እና የኢኮኖሚ ትብብር እየተጠናከረ የመጣ ሲሆን አገራችን በህንድ-አፍሪካ ፎረም ንቁ ተሳትፎ ታደርጋለች፡፡ በዚህም አገራችን በሁለተኛው የሕንድ አፍሪካ ፎረም ወቅት ካቀረበቻቸው ፕሮጀክቶች መካከል ሁለት ተቋማት ማለትም Bare foot Vocational Training center

እና Information Technology Center፣ እንዲሁም በክልል ደረጃ Farm Science Center በአገራችን እንዲገነቡ ማስወሰን ተችሏል፡፡ በተጨማሪም ህንድ በስኳር ልማት ዘርፍ ለአገራችን ብደር ያቀረበች ሲሆን የህንድ ባለሃብቶችም በተለያዩ የኢኮኖሚ ዘርፎች ተሰማርተዋል፡፡

ቻይና ከአገራችን የልማት አጋሮች መካከል አንዷ እና ዋነኛዋ ስትሆን ባለፉት አስር አመታት የአገራቱ ግንኙነት ተጨባጭ ውጤት አሳይቷል፡፡ የኢትዮጵያ እና ቻይና ወዳጅነት ወደ "አጠቃላይ ስትራቴጂያዊ ትብብር ወዳጅነት" (Comprehensive Strategic Cooperative Partnership) ከፍ ብሏል። አገራችን የ Asia Infrustructure Investment Bank/AIIB/ ሙሉ አባል እንድትሆን ተደርጓል። በአገራችን የኢንቨስትመንት እና መሰረተ ልማት ግንባታ ዘርፍ የተሰማሩ የቻይና ኩባንያዎች ቁጥር በየጊዜው እየጨመረ ነው፡፡ ከቻይና የገንዘብ ተቋማት ጋር ጠንካራ ግንኙነት የተፈጠረ ሲሆን የጅቡቲ-አዲስ አበባ የምድር ባቡርን፣ የስኳር ልማት ፕሮጀክቶችን እና የኤሌክትሪክ ሃይል ማመንጫ ግድቦችን ጨምሮ ሌሎች የልማት ስራዎችን ለመገንባት የዋለ የገንዘብ ብድር ከቻይና ተገኝቷል፡፡ በተጨማሪ ከቻይና ጋር በትምህርት፣ በባህል፣ በግብርና እና ሌሎች ዘርፎች ዘርፈ ብዙ የትብብር መስመሮች ተዘርግተዋል፡፡ በዚህም ኢትዮጵያ  በውጭ ግንኙነት እና የልማት ትብብር ዘርፍ በቻይና እንደ ሞዴል ከተመረጡ 3 አገሮች መካከል አንዷ ሆናለች፡፡

የኢትዮ-ቻይና የጋራ ኮሚሽን 8ኛው ስብሰባ እ.ኤ.አ ሚያዝያ 10 ቀን 2014 በአዲስ አበባ ተካሄዷል፡፡ የቻይና መንግስት የአፍሪካ እና እስያ የልማት ቀጠና ለመፍጠር ባቀረበው ሃሳብ የአገራችንን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ስራዎች እየተከናወኑ ይገኛል፡፡ ባለፉት አስር አመታት ሶስት የቻይና አፍሪካ የትብብር ፎረሞች የተደረጉ ሲሆን ሁሉም መድረኮች ንቁ ተሳትፎ የተደረገባቸው እና በአፍሪካ እና ቻይና ግንኙነት ላይ መሪ አቅጣጫዎችን በማስቀመጥ ከፍተኛ ሚና የተጫወቱ ናቸው፡፡

## 2.ባለብዙ ወገን አለም አቀፍ መድረኮች

አገራችን ከLeague of Nations መመስረት ጀምሮ በአለም አቀፍ መድረኮች እና ተቋማት ስታከናውን የቆየችው ተሳትፎ ባለፉት አስር አመታትም ተጠናክሮ ቀጥሏል፡፡

### ሀ/የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የጸጥታ ምክርቤት

አገራችን እ.ኤ.አ ጃኑዋሪ 2017 ጀምሮ የ.ተ.መ.ድ የጸጥታው ምክር ቤት ተለዋጭ አባል በመሆን ለሁለት አመታት ተመርጣለች፡፡ አገራችን የአፍሪካ ህብረት እጩ ሆና መቅረቧ እና በከፍተኛ የድምጽ ድጋፍ ተለዋጭ አባል ሆና መመረጧ በሰላም እና ደህንነት መስክ ላደረገችው አስተዋጽኦ እውቅና የተሰጠበት ነው፡፡ ይህን ስኬት ለማስመዝገብ በተ.መ.ድ አባላት መካከል የተደረጉ ቅስቀሳዎች እና አገራችን በሰላም እና ደህንነት መስክ በክፍለ አለሙ እና በአፍሪካ ውስጥ ያበረከተቻቸው ጉልህ አስተዋጽኦዎች ትኩረት እንዲሰጣቸው ለማድረግ የተሰሩት ስራዎች ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል፡፡ የምክር ቤቱ አባል መሆናችን የአገራችን እንዲሁም የአፍሪካ የሰላም እና ደህንነት ፈተናዎች ተገቢው ትኩረት እንዲሰጣቸው እና መፍትሄ እንዲያገኙ ለማድረግ ይረዳል፡፡ በተጨማሪ የም/ክርቤቱን አሰራር እና ውሳኔዎች በቅርበት በመከታተል በሰላም እና ደህንንት መስክ አገራችን ወደፊት የምታደርጋቸውን እንቅስቃሴዎች ለማጎልበት ከፍተኛ ሚና ይኖረዋል፡፡

### ለ/የአፍሪካ ህብረት

አገራችን የአፍሪካ አንድነት ድርጅት እንዲመሰረት ከፍተኛ ድርሻ ያላት የአፍሪካ ህብረት መስራች አባል እንዲሁም የህብረቱ ኮሚሽን አስተናጋጅ አገር እንደመሆኗ ህብረቱ የተቋቋመበት አላማ እንዲሳካ የምታደርገው ከፍተኛ ጥረት ባለፉት አስር አመታት ተጠናክሮ ቀጥሏል፡፡ በዚህ መሰረት አገራችን አዲሱ የአፍሪካ ሕብረት ፅ/ቤት ተጀምሮ እስከሚያልቅ ከፍተኛ ድጋፍ ሰጥታለች፣ በ 2013 ዓ.ም. የአፍሪካ ህብረት 50ኛ ዓመት የምስረታ በዓል በመዲናችን በደማቅ ሁኔታ ተከብሯል እንዲሁም ባለፉት አስር አመታት የህብረቱን የመሪዎች ጉባኤዎች እና ሌሎች ስብሰባዎች አስተናግዳለች፡፡

አገራችን በህብረቱ ያላትን ግንባር ቀደም ሚና በማስቀጠል የአዲስ አጋርነት ለአፍሪካ ልማት (NEPAD) የአፍሪካ የእርስ በርስ መገማገሚያ መድረክ (APRM) እንዲሁም የህብረቱ የአየር ንብረት ለውጥ የመሪዎች ኮሚቴ (CAHOSCC) አባል እና ሰብሳቢ በመሆን አገልግላለች፡፡ በወቅቱ እየተከናወነ ባለው የህብረቱ የለውጥ ትግበራ ስራ ላይም በንቃት በመሳተፍ ላይ ትገኛለች፡፡ በተጨማሪ የአፍሪካ እና የጥቁር ህዝቦችን ታሪክ በመቀመር፣ በማጥናት እና ምርምሮችን በማከናወን ላይ የሚሰማራው የመላው አፍሪካ ጥናት ዩኒቨርሲቲ በአድዋ ላይ እንዲቋቋም ሃሳብ በማቅረብ ሙሉ ድጋፍ ተገኝቷል፡፡

## 3. የአየር ንብረት ለውጥ አለም አቀፍ ስምምነቶች ድርድር

አገራችን በአለም አቀፍ ደረጃ የሚደረጉ የአየር ንብረት ለውጥ ስምምነቶች እና የሙቀት መጨመርን ለመግታት እና ያደሰረውን ጉዳት ለመቀልበስ እና የመቋቋም አቅምን ለመገንባት የሚቀረጹ ፕሮግራሞች የአፍሪካ ሃገራትን ልዩ ሁኔታ እና ተጋላጭነት ከግምት ያስገባ እንዲሆን ከፍተኛ ጥረት ስታደርግ ቆይታለች፡፡ በኮፐን ሃገን እና ካንኩን በተደረጉት ጉባኤዎች አፍሪካ ለችግሩ ያደረገችው አስተዋጽኦ አለመኖሩ ታውቆ ለአህጉሪቱ የሚደረገው ድጋፍ ልዩ ቦታ ሊሰጠው እንደሚገባ የአፍሪካ ተደራዳሪ ቡድን መሪ በመሆን የአህጉሪቱን ጥቅም አስተጋብታለች፡፡

የፓሪስ የአየር ንብረት ለውጥ ስምምነት ድርድር በሚደረግበት ወቅትም ንቁ ተሳትፎ በማድረግ ስምምነቱ የታዳጊ አገራትን ጥቅም ያስከበረ እንዲሆን የዲፕሎማሲ ስራዎች ተከናውነዋል፡፡ ስምምነቱ ከተፈረመ በኋላም በ2016 በማራከሽ ሞሮኮ በተደረገው የአየር ንብረት ለውጥ ጉባኤ ኢትዮጵያ በመልማት ላይ ያሉ አገራት ቡድንን ለሁለት አመታት እንድትመራ ተመርጣለች፡፡

የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ በአየር ንብረት ለውጥ ድርድሮች ላይ ባደረጉት ከፍተኛ አስተዋጽኦ በተ.መ.ድ ዋና ፀሐፊ ከቀድሞ የኖርዌይ ጠቅላይ ሚኒስትር ጋር ተመርጠው የአየር ብክለትን ለመቋቋም የሚያስችል የፋይናንስ ሀብት ለማሰባሰብ ሀሳብ እንዲያመነጭ ያቋቋሙትን High-Level Advisory Group On Climate Change Financing እንዲመሩ መሰየማቸው የሚታወስ ሲሆን፣ የዚህ አማካሪ ቡድን ሪፖርትን መሠረት በማድረግ የአለም

አቀፉ ህብረተሰብ የ Green Climate Fund ለማቋቋም ችሏል፡፡ እነዚህ ተግባራት አገራችን ላይ ዘርፈ ብዙ ፈተና ለፈጠረው የአየር ንብረት መዛባት ከአለም አቀፉ ማህበረሰብ ጋር በመስራት የመፍትሄው አካል መሆን የተቻለበት እና ውጤት የተገኘበት የዲፕሎማሲ ተግባር ነው፡፡

## 4.ፍልሰት እና ስደተኞች

አገራችን በዋናነት ከኤርትራ፣ ደቡብ ሱዳን እና ሶማሊያ የሚመጡ ስምንት መቶ ሺህ የሚደርሱ ስደተኞችን በማስተናገድ ከአፍሪካ አንደኛ ከአለም አምስተኛ የስደተኛ ተቀባይ አገር ናት፡፡ ይህን አለም አቀፍ ሃላፊነቷን ለመወጣት ከተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽነር ፣ ከዓለም አቀፉ የፍልሰት ድርጅት እና ከበለጸጉ አገራት ጋር በቅርበት ስራዎች ተከናውነዋል፡፡

አገራችን የስደት እና የፍልሰት ምንጭ የሆኑ ችግሮች በዘላቂነት የሚፈቱበትን ሁኔታ በማመለካከትም ሃላፊነቷን በመወጣት ላይ ትገኛለች፡፡ በዚህም ረገድ አለመግባባቶች በሰላማዊ መንገድ እንዲፈቱ፣ አገራት በድህነት ቅነሳ ላይ እንዲያተኩሩ፣ ለወጣቶች የትምህርት እድል እና ስራ ፈጠራ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶት የተሻለ ህይወት ፍለጋ አገራቸውን ለቀው የሚወጡ ወጣቶች ቁጥር እንዲቀንስ በተገኘው አጋጣሚ ቅስቀሳ ታደርጋለች፡፡ በዚህ ረገድ በኢትዮያ እና አውሮፓ አጋርነት ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቷቸው ከተሰሩ ተግባራት መካከል ከምስራቅ አፍሪካ ወደ አውሮፓ የሚደረገው መደበኛ ያልሆነ የሰዎች ፍልሰት ሲሆን አገራችን ከህብረቱ አገራት ጋር ለመተባበር የሚያስችሏት Common Agenda for Migration and Motility እና Valletta Plan of Action ተፈርሟል፡፡ እነዚህ ሰነዶች ሕገወጥ የሰዎች ዝውውርን ለማስቆም እና መደበኛ ላልሆነ ፍልሰት መሰረታዊ ምክንያት የሆነውን ድህነትን እና ስራ አጥነትን ለመፍታት በማሰብ ተጨባጭ የመፍትሄ ሃሳቦችን ያስቀመጠ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አገራችን በ2016 የአፍሪካ ቀንድ አገራት እና አውሮፓ ህብረትን የያዘው የKhartoum Process ሊቀመንበር ሁና ተመርጣለች፡፡ በተጨማሪም በ2016 በአሜሪካ ፕሬዝዳንት ሰብሳቢነት በተካሄደው የስደተኞች ስብሰባ ላይ በመሳተፍ ችግሩን ከመሰረቱ ይፈታል የተባለውን ተገንብተው ለስደተኞች እና ለስደተኛ አስተናጋጅ ማህበረሰቦች የስራ እድል የሚፈጥሩ የኢንደስትሪ ፓርኮች ግንባታ ሃሳብ አቅርባለች፡፡

ሃሳቡ ተቀባይነት አግኝቶ የበለጸጉ አገራት የሚያደርጉትን የገንዘብ ድጋፍ በመስጠት ላይ ይገኛሉ፡፡

## 5.የዲፕሎማሲ ማእከልነትን ማጠናከር

አዲስ አባባ የዲፕሎማሲ መዲናነቷን እንድትወጣ ከማድረግ አንጻር የተለያዩ ተግባራት የተከናወኑ ሲሆን የአፍሪካ ህብረት አዲስ ጽ/ቤቱን ሲያስገነባ ከፍተኛ ድጋፍ ተደርጓል፣ የተ.መ.ድ የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን በአዲስ አበባ ያለውን ጽ.ቤቱን ለማስፋፋት ለሚያከናውነው ስራ ድጋፍ እየተደረገ ይገኛል፡፡ በተጨማሪ በክልሉና በአህጉሩ ለመንቀሳቀስ የሚፈልጉ ዓለምአቀፍ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጽ/ቤቶቻቸውን በአዲስ አበባ ለመክፈት ያቀረቡትን ጥያቄ በመመርመር ባለፉት አስር አመታት 93 አለም አቀፍ እና አህጉራዊ ድርጅቶች በከተማችን ጽ/ቤታቸውን ከፍተዋል፡፡ በዚህም አዲስ አበባ የተ.መ.ድ 3ኛ ግዙፍ የዲፕሎማቲክ መናሃሪያ ለመሆን በቅታለች፡፡

## 6.የገጽታ ግንባታ ስራዎቻችን

የአገራችን የሚዳሰሱ እና የማይዳሰሱ ቅርሶች በአለም አቀፍ ደረጃ ተገቢውን እውቅና እንዲያገኙ እና ለቱሪዝም ዘርፉ መጠናከር እና ለገጽታ ግንባታ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳለው በማመን ባለፉት አስር አመታት ቅርሶችን በአለም የቅርሶች ሃብት መዝገብ እንዲሰፍሩ ለማድረግ በተደረገው ጥረት የመስቀል በአል አከባበር፣ የገዳ ስርዓት፣ እና የጨምበላላ ስርአቶች በአለም ቅርስነት እንዲመዘገቡ ለተከናወነው ስራ የዲፕሎማሲ ድጋፍ ተሰጥቷል፡፡ በተጨማሪም አገራችን ለ20 አመታት ያከናወነቻቸው ስራዎች በማጉላት እና በማስተዋወቅ የሰሜን ተራሮች ብሄራዊ ፓርክ አደጋ ላይ ካሉ የአለም ቅርሶች መዝገብ እንዲወጣ ተደርጓል፡፡ እነዚህ ስራዎች በተለያዩ የመንገስት አካላት መካከል ውጤታማ ቅንጅት የተደረገባቸው ናቸው፡፡

## 7.ጉድኝቶችን በመመስረትና በማጠናከር ተጠቃሚነታችንን ማሳደግ

የጉድኝት ስራዎች በሀገር ውስጥ ፍላጎት ላይ ተመስርተውና ከጉድኝቶቹ ሊገኙ የሚፈለጉት ጥቅሞችን በመለየት የተለያዩ ተቋሞችን የማስተሳሰር ስራ ተከናውኗል፡፡ በዚህም 320 የሚሆኑ የተቋማት( ፓርላማ ለፓርላማ፣

የከተሞች፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ወዘተ) በውጪ ከሚገኙ አቻዎቻቸው ጋር ለማጎዳኘት ተችሏል፡፡

ጉድኝቶችን በማጠናከር ረገድ ከጉድኝቶቹ ተጨባጭ የሆኑ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ የልምድ ልውውጥ በማድረግ የምርምር ውጤቶችና ጥቅሞችን ማስገኘት ተችሏል።

ለአብነት ያህል፡- ሳኡዲ ሹራ ካውንስል ሀ/ተ/ም/ቤት ህንጻ ማስገንቢያ በገባው ቃል መሰረት 50 ሚሊየን ዶላር ድጋፍ ማድረጉን ፣ ከሎስአንጀለስ University of Southern California ጋር በተጀመረው ግንኙነት መሠረት Global Environmental and Occupational Health (GEO-Health) Hub በአገራችን ለመመሥረት የ3 ሚሊዬን የአሜሪካን ዶላር የሚያወጣ ፕሮጀክት ድጋፍ ለማስገኘት ተችሏል፡፡ በተጨማሪም ከጣሊያን የትምህርትና ህክምና ቁሳቁስ እንዲሁም የንጹህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት የሚውል ድጋፍ፣ ከNational Universtiy of Galway Irealand ለ5 ተማሪዎች በኢንጂነሪንግ ዘርፍ የPHD የትምህርት እድል፣ ከደ.ኮሪያ የስልጠና ዕድልና የልምድ ልውውጥ፣ 14 መኪናዎች ለጅማ ዩንቨርስቲ፣ የላቦራቶሪና የህክምና እቃዎች፣ ለምርምር የሚረዱ ማቴሪያሎች ድጋፍ እንዲገኝ ለማድረግ ተችሏል፡፡

## 8.የቢዝነስ እና ኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ

ባለፉት አስር አመታት አገራችን ከውጭ የምታገኘውን የኢንቨስትመንት ፍሰት፣ የውጭ ንግድ፣ የቴክኖሎጂ ሽግግር፣ ቱሪዝም እና የልማት ፋይናንስ ለማሳደግ ሰፊ ስራዎችን አከናውኗል፡፡ ይህንንም ለማሳካት አገራዊ የኢኮኖሚና የቢዝነስ የቅንጅት መድረክ በማቋቋም የአምስቱም ዘርፎች ሥራዎች እንዲሳለጡና የገጠሟቸው ማነቆዎች እንዲፈቱ ወሳኝ ሚና ተጫውቷል፡፡ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ መስክ ትኩረት አድርጎ የተንቀሳቀሰባቸው አምስቱ ዘርፎች፡-

### 8.1. በውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት ማስፋፋት ዘርፍ የተመዘገቡ ውጤቶች

ለተለያዩ አገራት የቢዝነስ ማህበረሰብ አባላት ስለ አገራችን የኢንቨስትመንትና ቢዝነስ ዕድሎች በአብዛኛው ገለፃዎች እንዲሰጡና የአንድ

በአንድ ምልመላዎች እንዲካሄዱ ማድረግ ተችሏል፡፡ ከምልመላ በተጨማሪ የውጭ ባለሃብቶች ወደ ኢንቨስትመንት ትግበራ እንዲሸጋገሩ ድጋፍ ተደርጎላቸዋል፡፡ አገራችን የቅድሚያ ትኩረት በምትሰጣቸው መስኮች ያለውን አማራጭ ጉብኝት ካደረጉ 5458 ከተለያዩ አገራት የመጡ ኩባንያዎች መካከል 2031 ኩባንያዎች ወደ ኢንቨስትመንት ትግበራ ተሸጋግረዋል። ከእነዚህ ኩባንያዎች መካከል ሰፊ የስራ ዕድል መፍጠር የሚችሉ፣ ሌሎችን መሰል ኩባንያዎች መሳብ የሚችሉና ኢንቨስትመንታቸው እውን ሲሆን በአገራችን ኢኮኖሚ ዕድገት ላይ ጉልህ አስተዋጽኦ ማበርከት የሚችሉ 152 ግዙፍ ኩባንያዎች ያለ ምንም መጉላላት መንግስት ባስገናባቸው የኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ ገብተው ኢንቨስት እንዲያደርጉ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ትኩረት በመስጠት እንቅስቃሴ አድርጓል፡፡ በተሰራው የቢዝነስ ዲፕሎማሲ የቻይናው Huajan Shoes የቱርኩ Ayka Addis፣ የህንዱ፣ Rymond፣ የስዊዲኑ H&M ፣ የእንደግሊዞቹ Diageo፣ Heineken፣ Unileiver የአሜሪካው General Electric እንደዚሁም ናይጄሪያው Dangote የመሳሰሉ ኩባንያዎች በአገራችን መዋእለ ነዋያቸውን እያፈሰሱ ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት በውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት

- ከቻይና 16.979 ቢሊዮን ብር ካፒታል ካስመዘገቡ 849 ፕሮጀክቶች መካከል 481 ወደሥራ ገብተው ለ32,354. ቋሚ እና 30,403 ጊዚያዊ የስራ እድል ፈጥረዋል፡፡ 254 ፕሮጀክቶች ወደሥራ ለመግባት ዝግጅት ላይ ናቸው፡፡
- ከቱርክ 7.773 ቢሊዮን ብር ካፒታል ካስመዘገቡ 155 ፕሮጀክቶች መካከል 84 ፕሮጀክቶች ወደሥራ ገብተው ለ11,278. ቋሚ እና 5,002 ጊዚያዊ የስራ እድል ፈጥረዋል፡፡ 34 ፕሮጀክቶች ወደሥራ ለመግባት ዝግጅት ላይ ናቸው፡፡
- ከሳዑዲ አረቢያ 5.987 ቢሊዮን ብር ካፒታል ካስመዘገቡ 73 ፕሮጀክቶች መካከል 17 ፕሮጀክቶች ወደሥራ ገብተው 1,910 ቋሚ እና 20,802 ጊዚያዊ የስራ እድል ፈጥረዋል፡፡ 17 ፕሮጀክቶች ወደሥራ ለመግባት ዝግጅት ላይ ናቸው፡፡
- ከህንድ በ5.417 ቢሊዮን ብር ካፒታል ያስመዘገቡ 268 ፕሮጀክቶች መካከል 136 ፕሮጀክቶች ወደሥራ ገብተው ለ7,171. ቋሚ እና 9,381

ጊዜያዊ የስራ እድል ፈጥረዋል፡፡ 38 ፕሮጀክቶች ወደሥራ ለመግባት ዝግጅት ላይ ናቸው፡፡

ባለፉት አስር አመታት ከአገራችን የግል ሴክተር ማህበረሰብ ጋር በመቀናጀት በአገር ውስጥና በውጭ አገር 101 የኢኮኖሚና ቢዝነስ ፎረሞችን በማዘጋጀት የአገራችንን የኢንቨስትመንት አማራጮች ለውጭ ኩባንያዎች በስፋት የማስተዋወቅ ስራ በቋሚነት እየተሰራበት ሲሆን ፎረሞቹን በመጠቀም 1071 የአገራችን የግል ቢዝነስ ኩባንያዎች ከውጭ አገር አቻ ኩባንያዎች ጋር የቢዝነስ ትስስር እንዲፈጥሩ ማድረግ ተችሏል። በዚህም ከኢትዮጵያዊያን ጋር በሽርክና የተደረጉ ኢንቨስትመንቶች የኢትዮ-ሳዑዲ በግንባር ቀደምትነት የሚቀመጥ ሲሆን 4.41 ቢሊዮን ብር ካፒታል ያላቸው 76 ፕሮጀክቶች ወደሥራ ገብተው ለ8,769 ሰዎች ቋሚ እና ለ10,953 ሰዎች ጊዜያዊ የስራ እድል ተፈጥሯል፡፡ 38 ፕሮጀክቶችም ወደሥራ ለመግባት ዝግጅት ላይ ይገኛሉ፡፡

## 8.2. የወጪ ንግድ የገበያ ጥናት፣ ፕሮሞሽንና ትስስር

የውጭ ንግድን በሚመለከት በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ በዋናነት የተቀመጠው ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ ምርቶችን አይነት፣ ጥራትና መጠን በማሳደግ እና እሴት በመጨመር ለውጪ ገበያ ማቅረብ ሲሆን ባለፉት አስር አመታት የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ይህን አገር አቀፍ ግብ ለማሳካት ትኩረት ሰጥቶ ተንቀሳቅሷል፡፡ ከነባርና አዳዲስ የገበያ መዳረሻ ዕድሎች መካከል በዋነኛነት በአውሮፓ Everything but Arms (EBA)፣ በአሜሪካ African Growth & Opportunities Act (AGOA)፣ ቻይና እና ህንድ የኮታና ቀረጥ ነፃ ዕድሎች ተጠቃሚ በመሆን እና በአፍሪካና መካከለኛው ምስራቅ በተደረገ ገበያ የማፈላለግ ስራ ለጨርቃጨርቅ፣ ለቆዳና የቆዳ ውጤቶች፣ ለፍራፍሬ እና አበባ ምርት፣ ቡና እና የቅባት እህሎች ምርቶች ገበያ የማስፋት ሥራ ተከናውኗል።

ዋነኛ የውጭ ንግድ ምርቶቻችን እና ገዢዎቻችን ጋር ያለንን ግንኙነት ከማጠናከር በተጨማሪ በሁሉም ኤምባሲዎቻችን አዳዲስ የገበያ መዳረሻዎች እንዲፈጠሩ ጥረት የማድረግ ሃላፊነት በመስጠት የገበያ እድሎችን የማስፋት ሚናውን ተጫውቷል፡፡ በሌላ በኩል በአገራችን የተለያዩ አካላት የሚቀርቡ

የገቢ ምርቶች ግኘ መሰረት በማድረግ ልምዱና ብቃቱ ያላቸውን የውጭ አቅራቢዎች የማፈላለግ እና የማገናኘት ስራ ተከናውኗል፡፡

በአገራችን ያለውን የምርት ዕጥረትና የጥራት ችግር ለመቅረፍ በአቅም ግንባታ ላይ በማተኮር ከቻይና፣ ከጃፓን እና ከኔዘርላንድስ፣ ከስዊድንና ከጀርመን ጋር አበረታች ሥራ እየተሰራ ይገኛል፡፡ በተጨማሪ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በሚያስተባብረው በብሔራዊ የኢኮኖሚና ቢዝነስ የቅንጅት መድረክ ሥር በሚገኘው የውጭ ንግድ ማስፋፊያ መድረክ አማካኝነት ዘርፉ ላይ የሚያጋጥሙ ማነቆዎችን መፍታት ተችሏል፡፡

## 8.3. የቴክኖሎጂ ሽግግር

ባለፉት አስር አመታት የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የኢትዮጵያ የኢኮኖሚ እድገት ከቴክኖሎጂ ሽግግር ተጠቃሚ እንዲሆን አጋዥ ሚናን ተጫውቷል፡፡ በዚህ ረገድ፡-

- በአገራችን ኢንቨስት ያደረጉ ኩባንያዎች ከኢንቨስትመንታቸው ጋር በተያያዘ ለአገራችን የእውቀት ሽግግር እንዲያደርጉ የማግባባትና ሁኔታዎችን የማመቻቸት ስራ ተሰርቷል
- በተለያዩ አገራት ባሉ ኤምባሲዎቻችን አማካኝነት የአገራችን ኢንዱስትሪና መሰረተ-ልማት ኢንጂነሪንግ ዘርፎችን ተወዳዳሪ ለማድረግ በፍላጎት ላይ የተመሰረተ ተስማሚ የቴክኖሎጂ ሽግግር ለማሳለጥ አስፈላጊውን የመረጃ፣ ድጋፍ የማስተዋወቅ እና የማግባባት ሥራ በመስራት በአግሮ-ፕሮሰሲንግ ፣ በግብርና፣ በቴሌኮሙኒኬሽን፣ በጤና፣ በአምራች ኢንደስትሪ፣ ወዘተ ዘርፎች እንዲሸጋገሩ የበኩሉን ሚና ተጫውቷል፡፡ በዚህም የግብርና ምርምር ኢንስቲቲዩት፣ የመንገዶች ባለሥልጣን፣ ከተማ ልማት፣ ቤቶችና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር፣ የማዕድን ሚኒስቴር፣ የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲቲዩት እና የምድር ባቡር ኮርፖሬሽን የቴክኖሎጂ ፍላጎቶችን በማሰባሰብ ተፈላጊ ቴክኖሎጂዎችን ወደአገራችን ማሸጋገር ተችሏል፡፡
- ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ትብብር ሚኒስቴር፣ ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጠን፣ ልማት ባንክ፣የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ጋር በመመካከር በአምራች ኢንደስትሪ ዘርፍ እሴት በማከል የዘርፉን አቅም የሚያሳድጉ ባለሃብቶች የማበረታቻና ማትጊያ ሥርዓት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ድጋፍ ተደርጓል፡፡

- የውጭ ጉዳይ በሚያስተባብረው ብሔራዊ የኢኮኖሚና ቢዝነስ የቅንጅት መድረክ ሥር በሚገኘው የቴክኖሎጂ ሽግግር ኮሚቴ አማካኝነት ለክልል አደረጃጀቶች፣ ለግል ባለሃብቱና ለመንግስት ስራ ሃላፊዎች በቴክኖሎጂ አማራጭ መንገዶች ዙሪያ የአቅም ግንባታና የቴክኒክ ድጋፎች የተሰጡ ሲሆን በቴክኖሎጂ ሽግግር ሂደት ያጋጠሙ የአሰራር ማነቆዎች እንዲፈቱ ስራዎች ተከናውነዋል
- በቴክኖሎጂ ዘርፍ የተገኙ የሥልጠና ዕድሎች ለሚመለከታቸው የባለድርሻ አካላት እንዲደርሳቸው አስፈላጊው ድጋፎችና መረጃዎች ተደርጓል፡፡

## 8.4. የቱሪዝም ማስፋፋትን በተመለከተ

አገራችን ካላት የተፈጥሮ፣ የባህል እና የታሪክ ቱርስት መስህብ አንፃር ከቱሪዝም ኢንዱስትሪው ተጠቃሚነቷን በማረጋገጥ ዘርፉ ለአገራችን እድገት ጉልህ ሚና እንዲጫወት የተቀመጠውን አገራዊ ግብ ለማሳካት የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ባለፉት አስር ዓመታት የቱሪዝም ፍሰቱ እንዲጨምርና ከዘርፉ ጋር ተያያዥነት ያላቸው የውጭ እንቨስትመንቶች እንዲበራከቱ ለማድረግ ከባለድርሻ አካላት ጋር እንቅስቃሴ አድርጓል፡፡ በአገራችን ጉብኝት ያደረጉ የውጭ ቱሪስቶች ፍሰት ያሳየውን ዕድገት ስንመለከትም በ2003 ከነበረው 508,995 የውጭ የጎብኝዎች ቁጥር በ2006 ወደ 724,220 ያደገ ሲሆን ከዘርፉ የተገኘው ገቢም 1.19 ቢሊዮን ዶላር ደርሷል፡፡ ይህን ውጤት ለማስመዝገብ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ካከናወናቸው ተግባራት መካከል

- በተለያዩ አገራት በተዘጋጁ 203 የቱሪዝም ትርኢቶችና ኤግዝብሽኖች ላይ ተሳትፎ እነዲደረግ በኤምባሲዎቻችን የማስተባበር ስራ ተከናውኗል
- 1179 የቱር ኦፕሬተሮች አገራችንን በቱር ፓኬጃቸው ውስጥ እንዲያካትቱ ማድረግ ተችሏል
- በብሔራዊ የኢኮኖሚና ቢዝነስ የቅንጅት መድረክ ሥር በሚገኘው የቱሪዝም ማስፋፊያ የዘርፍ መድረክ አማካኝነት በዘርፉ ያጋጠሙ ችግሮች የሚፈታበት መንገዶች ተቀይሰዋል

## 8.5. የልማት የገንዘብ አቅርቦት

ባለፉት አስርት አመታት  የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ መስክ ትኩረት አድርጎ ከተንቀሳቀሰባቸው ጉልህ ክንዋኔዎች መካከል የልማት የገንዘብ ድጋፍ ማስገኘት አንዱ ነው፡፡ ከገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር እና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን በወቅታዊ የሁለትዮሽ እና የባለብዙ ወገን የልማት ትብብር አለቃቀቅ ፣ በትብብሩ አፈፃፀምና አዳዲስ ፋይናንስ በማስገኘት ረገድ በተካሄዱ የጋራ ኮሚሽን ፎረሞች፣ የምክክር ስብሰባዎች እና ድርድሮች ላይ ከፍተኛ ተሳትፎ አድርጓል፡፡

- ከአለም አቀፍ የፋይናንስ ተቋማት የሚገኙ ብድሮችንና እርዳታዎችን በዋሽንግተን፣ በብራስልስ፣ በኩዌት፣ በካርቱም፤ ከተ.መ.ድ. የተለያዩ አካላት የሚገኙ ትብብሮችን በኒዮርክ፣ በጄኔቫ፣ በሮም፣ በፓሪስ፤ እንዲሁም ከባይላተራል ምንጮች የሚገኙ ትብብሮችን በለንደን፣ በቤጂንግ፣ በኒውደልሂ፣ በአንካራ፣ በርሊን የኢትዮጵያ ኤምባሲዎች፣ ቋሚ መልክተኛ ጽ/ቤቶቻችን ትኩረት ሰጥተው እንዲንቀሳቀሱባቸው በማድረግ ውጤታማ ሥራ መስራት ተችሏል፡፡
- በዚህ መሰረት በአስር ዓመታት ውስጥ ከእርዳታና ብድር የተገኘው የገንዘብ መጠን 22.5312 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ደርሷል።
- ከተገኘው የልማት ፋይናንስ ድጋፍ 18, 412, 626, 220 የአሜሪካን ዶላር በማስለቀቅ ለተለያዩ ትልልቅ ፕሮጀክቶች፣ መሰረተ ልማቶች፣ ለትምህርት፣ ጤና ዘርፎች እድገት እንዲውሉ ተደርጓል። ከዚህ የልማት ትብብር ውስጥ 17.641 ቢሊዮን ገንዘብ በGTP 1  የእቅድ ዘመን የተገኘ ሲሆን በወቅቱ ከተገኘው የልማት ፋይናንስ ድጋፍ 11.14 በሊዮን የአሜሪካን ዶላር እንዲለቀቅ  በተመረጡ አገሮች የሚገኙ ኤምባሲዎቻችን ርብርብ ከፍተኛ ነበር፡፡
- ከተመድ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ፈንዶች፣ ፕሮግራሞች እና ፕሮጅክቶች (ECOSOC,DESA, IOM,UNHCR) ተጠቃሚነታችንን በይበልጥ ለማሳደግ በጥናት ላይ የተመሰረተ እንቅስቃሴ ተደርጓል
- አገራችን ያጋጠማትን ድርቅ መቋቋም እንዲቻል ለጋሽ ድርጅቶች የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ በማግባባት የአለም ምግብ ፕሮግራም ኤክስኩቲቭ ቦርድ ተጨማሪ በጀት እንዲመድብ ለማድረግ ተችሏል

## 8.6. ዳያስፖራው የኢኮኖሚ ተሳትፎ

ዳያስፖራው በቢዝነስና ኢንቨስትመንት እንዲሳተፍ ለማድረግ በተደረገው እንቅስቃሴ ባለፉት አስር ዓመታት 5161 የዳያስፖራ አባላት በሁሉም ክልሎችና የከተማ አስተዳደሮች በተለያዩ የኢንቨስትመንት መስኮች እንዲሰማሩ ድጋፍ ተደርጓል፡፡

ዳያስፖራው ወደአገር ውስጥ የሚልከውን ገንዘብ ለማሳደግ የሃዋላ አገልግሎትን ለመጨር የሚያስችል መመሪያ በብሄራዊ ባንክ ተቀርጿል፡፡ በተጨማሪ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በአገራችን በሚገኙ ባንኮች የውጭ ምንዛሪ አካውንት እንዲከፍቱና እንዲያንቀሳቅሱ ብሔራዊ ባንክ እ.ኤ.አ 2006 አሻሽሎ ባወጣው መመሪያ መሠረት ከ25 ሺህ በላይ የውጭ ምንዛሪ አካውንቶች የተከፈቱ ሲሆን በእነዚህ ሂሳቦች 153 ሚሊዮን 816 ሺህ የአሜሪካን ዶላር ተቀማጭ ተደርጓል፡፡ እ.ኤ.አ. በ 2010 1.8 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር የነበረው ወደ አገር ውስጥ የተላከ ገንዘብ እ.ኤ.አ. 2015/2016 ወደ 4.1 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር አድጓል፡፡ ይህም በሃዋላ አስተላላፊዎች እየተላከ ያለው የውጭ ምንዛሪ አገራችን ከቀጥተኛ የልማት ፋይናንስ (ODA) እና ከቀጥተኛ የውጭ ኢንቨስትመንት (FDI) የምታገኘውን የውጭ ምንዛሪ ብልጫ አሳይቷል፡፡ በተጨማሪ ሕጋዊ የገንዘብ ማስተላለፊዎችን ለማበረታታት በገንዘብ ማስተላለፍ ዙሪያ በሚስተዋሉ ችግሮችና የመፍትሄ ሃሳቦች ላይ ጥናት ተካሂዶ ውጤቱ ቀርቧል፡፡ ጥናቱ ተግባራዊ ሲሆን፣ የውጭ ምንዛሪ ፍሰቱ የበለጠ እንደሚያድግ ይጠበቃል፡፡

ለታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ የሚውል ፋይናንስ ከዳያስፖራው ለማሰባሰብ የቦንድ ሽያጩንና ድጋፍ አሰባሰቡን የሚያስተባብሩ 77 ምክር ቤቶች በተለያዩ አገሮች እንዲቋቋሙና 144 ነባር የህዳሴ ምክር ቤቶች እንዲጠናከሩ ተደርጓል፡፡ በዚሁ መሰረት ከ42 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር በላይ ከቦንድ ግዢና ስጦታ መሰብሰብ የተቻለ ሲሆን በተባበሩት አረብ ኤሜሬቶች የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ለህዳሴ ግድቡ ድጋፍ ለማሰባሰብ የሚደረገውን ጥረት ለማገዝ ሁለት አውቶሞቢሎችን ገዝተው በስጦታ መልክ አበርክተዋል፡፡ የዳያስፖራውን ሙያዊ አስተዋጽኦ በሚመለከት ከ160 በላይ የሆኑ በተለይም የከፍተኛ ኢንጂነሪንግ ሙያ ያላቸው የዳያስፖራ አባላት ለግድቡ ግንባታ በተደራጀ መልክ ሙያዊ አስተዋጽኦ ለማበርከት እ.ኤ.አ. በ2013 Ethiopian International

Professional Support for Abay በሚል ማህበር በማቋቋም ሙያዊ ምክር በመስጠትና የግድቡን ግንባታ የሚመለከቱ ሳይንሳዊ ጽሁፎችን በማዘጋጀት ተሳትፎ በማድረግ ላይ ይገኛሉ፡፡

የዕውቀት እና ቴክኖሎጂ ሽግግርን በተመለከተ 536 የዳያስፖራ አባላት በተለያዩ የሙያ መስኮች በአጭር፣ መካከለኛና ረጅም ጊዜ ስልጠና በመስጠት፣ በአገራችን የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በኮንትራትም ሆነ በቋሚነት ተቀጥረው በማገልገል፣ ወዘተ... መንገዶች በዕውቀትና ቴክኖሎጂ ሽግግር በመሳተፍ ላይ ይገኛሉ፡፡ የተለያዩ የሙያ አደረጃጀቶች በመፍጠር ተሳትፎ እያደረጉ ከሚገኙት መካከል Ethiopians in North America Health Professionals Association (ENAHPA)፣ Ethiopian Doctoral and Master Academy (EDMA)፣ Ethio-American Doctors Group፣ Science, Technology, Engineering and Maths (STEM)Team፣ People to People፣ Ethiopian International Professional Support for Abay፣ Association for Higher Education and Development (AHEAD)፣ Global Knowledge Exchange Network፣ Ethiopian Professional Network፣ Ethiopian Scientists Network (ESAN) በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ ማህበራቱ በከፍተኛ ትምህርት፣ በጥናትና ምርምር፣ በስልጠና፣ በቁሳቁስ ድጋፍ፣ ወዘተ... ከፍተኛ አስተዋጽኦ ማበርከት ችለዋል፡፡

በኒውዮርክና አካባቢው በሚኖሩ የዳያስፖራ አባላት የተቋቋመውና STEM የተባለ ስብስብ ከአዲስ አበባ እና ከአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲዎች፣ በለንደን የተቋቋመው EDMA ከጂማ እና ከባህርዳር ዩኒቨርሲቲዎች ጋር የጋራ ትብብር ስምምነት በመፈራረም በተቋማቱ የሚካሄዱ የማስትሬትና የዶክትሬት ፕሮግራሞችን በማገዝ ላይ የሚገኙ ሲሆን፣ ከ70 በላይ የህክምና ዶክተሮች የመሰረቱት Ethiopian American Doctors Group tertiary ደረጃ ሆስፒታል በመገንባት አዲስ አበባን የአፍሪካ Medical Art Center ለማድረግ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል፡፡

ፕሮፌሽናል የዳያስፖራ አባላት በተናጠልና በተደራጀ ሁኔታ በዕውቀትና ቴክኖሎጂ ሽግግር መስክ ትውልድ አገራቸውን በመደገፍ ላይ የሚገኙ ቢሆንም ያላቸውን ተነሳሽነትና ፍቃደኝነት ለማበረታታትና ለመደገፍ እንዲያስችል ዕውቀትና ቴክኖሎጂ ሽግግር ላይ ትኩረት አድርጎ ከሚሰራ Alliance for Brain-Gain and Innovative Development (ABIDE) ከተባለ አገር በቀል ድርጅት

ጋር በመተባበር Knowledge Diaspora Trust Fund ማቋቋም በማስፈለጉ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ ከትምህርት ሚኒስቴር፣ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እና ከሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የተውጣጣና ትረስት ፈንዱን የሚያቋቁምና የሚያስተዳድር አብይ ኮሚቴ ተቋቁሟል፡፡